ETHIOPIAN FREE-PRESS JOURNALISTS IN EXILE
በስደት ላይ የሚገኙ የኢትዮጵያ ነጻ-ፕሬስ ጋዜጠኞች
ድምፅ ለሌለው የኢትዮጵያ ህዝብ ድምፅ ነበርን!
We were the voice of voiceless Ethiopian people

January 25, 2012
No– 002/jan/12

# በጠመንጃ አስገዳጅነት የእውነት እጆች ቢታሰሩም፤ ህዝብ እውነታውን ይረዳል፤ ታሪክም ሃቅ ይፈርዳል!!

(በስደት ላይ ከሚገኙ የኢትዮጵያ ነጻ ፕሬስ ጋዜጠኞች የተሰጠ መግለጫ)
ጃኑዋሪ 25፣ 2012

በኢትዮጵያ ውስጥ ነጻ የሆነ አስተሳሰብ እንዲነግስ፤ በተለይ የኢትዮጵያ ነጻ ፕሬስ ጋዜጠኞች ታላቁን ሚናተጫውተዋል። ሃሳብን በነጻነት መግለጽ የአንድ ሰብዓዊ ፍጡር መሆኑንን፤ ይህም በአኩሪ ኢትዮጵያዊያን የትግልውጤት የተገኘ እንጂ፤ የኢህአዴግ ችሮታና ስጦታ እንዳልሆነ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው አሰምተዋል። አልፎተርፎም ስልጣን ከጠመንጃ ውስጥ በሚወጣ ጥይት ሳይሆን፤ ከምርጫ ሳጥን በሚገኝ የህዝብ ድምፅ መገኘትእንዳለበት በብዕራቸው ጫፍ መስክረዋል፤ አስተምረዋል። ይህን መሰረታዊ አስተሳሰብ መመሪያው አድርጎ ወደፊትየሚገሰግስ ህብረተሰብ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በመፈጠሩ፤ ለነጻነት የሚደረገው ትግል ወደፊት እንጂ ወደ ኋላየማይቀለበስበት ደረጃ ላይ ነው።

ላለፉት ሃያ አመታት የኢትዮጵያ ነጻፕሬስ ጋዜጠኞች ከፋፋይ የሆነውን የኢህአዴግ ዘረኛ አስተዳደርበማውገዛቸው ለህዝብ ያላቸውን ወገንተኝነት አረጋገጡ እንጂ፤ የአገራቸውን ጥቅም በግል ጥቅም የቀየሩበትአጋጣሚ ከቶ የለም። እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ፤ በስልጣን ላይ የሚገኘው አስተዳደር፤ ጋዜጠኞችን በአገር ክህደት፣በዘር ማጥፋት፣ ህዝብን በመንግስት ላይ በማነሳሳትና በሽብርተኝነት እየፈረጀ ጋዜጠኞችን ለእስር፣ ለእንግልትናለስደት መዳረጉን ይህ ትውልድ የሚመሰክረው ሃቅ ነው።

በ'ርግጥ ጋዜጠኞች፤ የገዢዎችን ጭንብል አውልቀው አጋልጠዋል፤ ከሃገር ጀርባ የሚፈጸሙትን ደባዎች አውግዘዋል። ይህ የእውነት ነበልባል የፈጀቻቸው፤ የሃቅ ብዕር ያቃጠላቸው አምባገነን ገዢዎች ግን እንቅልፍ የነሷቸውን የብዕር አርበኞች በሰበብ ባስባቡ ማሰር፣ ማንገላታት እና ከአገር እንዲወጡ ማድረግ ተቀዳሚተግባራቸው፣ ዋነኛ አማራጫቸው አድርገውታል።

የኢትዮጵያ ነጻ ፕሬስ ጋዜጠኞች የከፈሉትን መስዋዕትነት ለመረዳት ለሃያ አመታት የከተቧቸው ድርሳናትምስክሮች ናቸው። ለዚህ የጋዜጠኞች ውለታ የኢህአዴግ አስተዳደር "አሸባሪ" የሚል ቅፅል ሰጥቷቸው በማሰር፤ እውነት የሚናገሩ የፕሬስ ትሩፋቶችን ለማጥፋት የሞት ሽረት ግብግብ ላይ ይገኛል። ስለሆነምበሃሰት ክስ፣ በይስሙላ ፍርድ ቤት፣ ለሆዳቸው ባደሩ ዳኞችና ታማቂዎች እየተመሩ እውነትን ለመግደል ዛሬም ያለመታከት እየሰሩ ያሉትን ወገኖች አንድ ነገር ልናስታውሳቸው እንወዳለን። ወርቅ በእሳት እንደሚፈተነው ሁሉ፤ የኢትዮጵያ ነጻ ጋዜጠኞችም በእሳት ተፈትነዋል። በዚህም የ

እሳት ፈተናእንደጨርቅ አልነደዱም፤ እንደወርቅ አንጸባረቁ እንጂ። እነሆ በህዝብ ላይ የሚደርሰውን የግፍ በትርተጋሩ፤ መራር የሆነውን የመከራ ፅዋም ስለህዝብ ብለው ተጎነጩ። እነሱ ታሰሩ፤ እነሱ ተ ሰደዱ፤ተንገላቱም። ሃሳብን በነጻነት ለመግለጽ  የሚደረገው ትግል ግን፤ ከቶውኑም አይቋረጥም።

እነ እስክንድር ነጋ፣ ውብሸት ታዬ እና ርዕዮት አለሙ በሃሰት ክስ "አሸባሪ" ተብለው ለእስ ር ቤት ቢዳረጉም፤መላው ህዝብ እውነተኛ ማንነታቸውን ስለሚያውቀው፤ ነጻ ጋዜጠኞቻችን ከታሰሩበ ት የጨለማ ክፍሎች ውጪ፤ በሺዎች የሚቆጠሩ ደጋፊዎቻቸው ምን ጊዜም አብረዋቸው ይቆማሉ።

እንደሌሎች የኢትዮጵያ ነጻ ፕሬስ ጋዜጠኞች ሁሉ፤ እነሱም በእሳት የተፈተኑ ወርቆች በ መሆናቸው፤ ህዝብ ታላቅየኢትዮጵያዊነት ኒሻን ያጎናጽፋቸዋል። ከ'ንግዲህ ታሪክ እና ትውልድ የአምባ ገነኖችን ክፋት ሲያነሳ፤ በመሰዊያውገበታ ላይ የቀረቡ የኢትዮጵያ ነጻ ፕሬስ ጋዜጠኞችን ግን ከፍ አድርጎ በክብር ይዘክራቸዋል። ዛሬ በህግ ሽፋን ሃቅየሚናገሩ አንደበቶች ቢዘጉም፣ በጠመንጃ አስገዳ ጅነት የእውነት እጆች ቢታሰሩም፤ ህዝብ እውነታውን ይረዳል፤ ታሪክም ሃቅ ይፈርዳል።

ካለፉት ሃያ የነጻነት ትግል አመታት እንደተማርነው፤ ኢህአዴግ የተሸነፈ ሲመስለው ህዝባዊ ንቅናቄዎችንለመግታት ሲል ፍትህን ያዛባል፤ እጁም በደም ይነክራል። አሁንም በብዕር አርበኞች ላ ይ የወሰደው እርምጃሽንፈቱን እንጂ፤ መሪነቱን አያሳይም። በጠመንጃ አገዛዝ እና በህግ ሽፋን፣ በኢ ትዮጵያ ነጻ ፕሬስ ጋዜጠኞች ላይያደረሰውና እያደረሰ ያለው መከራም ተሸናፊነቱን ይበልጥ አጉልቶ ያሳያል። ኢህአዴግ የግፍ እና የበደል በትሩንባበዛው ቁጥር፤  የነጻ ፕሬስ ጋዜጠኞችንና የኢትዮጵያ ን ህዝብ የድል ነጥብ ከፍ ያደርገዋል። ይህ ፋይዳ ቢስ ክስ እናየሚሰጠውም ፍርድ አምባገነኖች በ ሽብር ቀፎን ውስጥ ለመሆናቸው ጉልህ ምስክር ነው።

እነሆ ኢህአዴግ በፍርሃትና በሽብር ውቅያኖስ ላይ ሲቀዝፍ፤ በነጻ አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ው ህዝባዊ መነቃቃት ደግሞ፤ የማያቋርጥ የጥሪ ደወሉን ከዳር እስከዳር እያስተጋባ፤ የነጻነት ትግሉን ይቀጥላል። ለዚህም ህዝቡ ከኢትዮጵያ ነጻፕሬስ ጋዜጠኞች ጎን በመቆም፤ የአንድነት ቃል ኪዳኑን እንዲያድስ  ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ዳዊት ከበደ
በስደት ላይ የሚገኙ የኢትዮጵያ ነጻ-ፕሬስ ጋዜጠኞች ሰብሳቢ።
678 437 5597